# ምነው ዳግም ጦርነት?

ተኮላ መኮንን
02/28/1999

የሳባ ጉዞ ምኞሽ ምንሊህን ይዞ ሲተም፣
ከፖርቹጊስ የጦር አጋር ከአሌክሳንደርያ ሥጋወደም።
ከቱርክ ከደርቡሽ ወረራ ከግራኝ መሐመድ ስግደት፣
ከቴዎድሮስ መቅደላ ከዮሐንስ የአንገት ስልበት፣
በሮም የዘርዓይ ድረስ ጎራዴ የሰላቶ ደም እልበት።

ለጣሊያን ነፍጥ በጋሻ ምቱሽ፣
ጀግናሽ ከግራ ቀኝ ሲመክትልሽ።

ድል በድል ሆኖ አደዋ ላይ እልል ተብሎ ሲፎከር፣
ምነው ምኒልህ ፈረሱ ባሕር አጠገብ አደሮ በነበር።
ወጫሌ የተሻረው ወል አደዋ መፍረሱ ቀርቶ፣
አዶሊስ ላይ በነበረ ግጫ ነቅሎ ቄጤማ አንጥፎ ውኃ ነክቶ።

ፈረንጅ በገባበት ሁሉ የተከለው ተንኮል ሴራ፣
ለዓመታት እኛም ላይ ሊያደራ?
እንደቆላ ቁስል ሊነፈርቅ እንደነቀርሳ ሊያንሰራራ?

ከከፋሽማ ተገንጠይ ካልጣመሽ ቤታችን ቤትሽ ባልን፣
ለትግሉ እንዳልደማን ለነሱ ትላንት እንዳልሞትን፣
ይቅር መቼስ ተብሎ የሆነ ያልሆነውን እንዳልቻልን፣
የሕዝቡን ቁጣ እንዳልገታን እሮሮውን እንዳልዋጥን፣
ሚስት እንደነጠቀ አጉራ ዘለል ጣውንትነት ሊከጅሉን?
በጥይት ለለበልቡን ባወሮፕላን ሊያቃጥሉን?
በሞርተር ሊጨፈጭፉን በታንካቸው ሊዳምጡን?

ተው ሲሏቸው ካልሰሙ አወሬው ከሆነ ንጉሳቸው፣
ሠላም ማለት አቅሯቸው ጦር ከሆነ ዳንከራቸው፣
ወንደሞቼ ምርጫም የለ ክንዳቸሁን አሳዩአቸው።

የተወጠረን ፊኛ እፍታ መች ይጎዳዋል፣
እስትንፋስማ ጌጡ ነው ወደ ሰማዩ ይወስደዋል።
ሲነኩት ነው እንጂ በመርፌ በበለዋ በጉጠቱ፣
የሚያምረው አወዳደቁ መሽመድመዱ አሟሟቱ።

ተዋቸው ሲባሉ ከነገሱ ይብቃ ሲሏቸው ካበጡ፣
ምንም ልመና አያሻም ወንደሞች የጠመቁትን ይጠጡ።
ሰሚ ካለ ግን ጦር ይብቃ በሏቸው ዘፈናቸውን ይቀይሩ፣

«አደየ ጀጋኑ» ይቅርና ስለፈቅር ይዘምሩ፣
ስለሰላም ተወያዩ በሏቸው መሃይሙን ያስተምሩ።

ከእጅ ወዳፍ የሚኖረውን ያንን ጭቁን አርሶአደር፣
ዛሬም ያላለፈለትን የከተማውን ላብ አደር፣
በግዴታ ተሰባስቦ የተከማቸውን ወታደር።
ምን አለ ሀሁ ቢያስተምሩት ሀ ግእዝ ለ ግዕዝ፣
የጦር ከበሮ ከመምታት የትም ክህት ክራር ከመጠረዝ፤

ምን አለበት «አሶ» ላይ በረባረቡ፣
ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ቢያቀርቡ፣
ሚግ እየገዙ በየሜዳው ከሚከስሩ።

ሰውን የማኅዳው ፍቅር እንጂ ጠቦማ መዝጊያ በር ነው፣
ትእግስት ሰላም ያዋቂ፤ ጡጫ ብትር የመሃይም ነው።

መሪዎች ትላንት ነበሩ አልፈዋል፤ የዛሬዎቹም ያልፋሉ፣
ምንም ነገር ቢፈጠር ሕዝቦች ግን ይኖራሉ።
እናም ለሚያልፈው ሕዝብ እትብቱን ለበጠሰ ሰው፣
ሠላምን እንስጠው እንጂ ጠላትነትን አናወርሰው።

ለምን ለምን እንቢ ካላችሁ፣
ከእውነት ይልቅ የዳንዴ ወሸት ከጣማችሁ፣
ለሃገር ሳይሆን ለግለሰብ ከቆማችሁ፣
የአማፃ ገነኑ ደንገጡሮች ከርከማቹን ያወላችሁ።